**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የሲቪል ዲቪዥን - አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች እና የማስታረቅ ቅርንጫፍ**
**510 4th Street, NW, Room 120, Washington, D.C. 20001**
**(202) 879-1120 | www.dccourts.gov**

# የደምዝ-ያልሆኑ ተቁራጮች እና ከተቆራጭ ነፃ የሆኑ የገንዘብ መጠኖች ላይ የባለዕዳ ማስታወሻ

በእርስዎ ላይ ፍርድ ቤት ፈርዶቦታል። ከእርስዎ ላይ ገንዘብ ተቀንሶ ዕዳው ሊከፈል ይችላል።

**መብትዎን ለማስጠበቅ ይሄንን በጥንቃቄ ያንብቡ።**

## ይሄንን ማስታወሻ የተሰጠኝ ለምንድን ነው?

በእርስዎ ላይ አንድ ተቋም ወይም ግለሰብ ክስ በመመስረት በፍርድ ቤት ውስጥ ተፈርዶላቸዋል። "Writ of Attachment" [**"የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የወጣ ተጨማሪ ማዘዣ"**] በሚባል ሰነድ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ አቅርበው ነበር እና የእርስዎን ገንዘብ ከሚያስቀምጠው ባንክ ወይም የእርስዎን ገንዘብ የያዘው ሌላ ግለሰብ ወይም ተቋም ላይ የፍርድ ቤት ማዘዣውን ልከውታል። ሰነዱ በእርስዎ ላይ የተመሰረተውን ክስ ላሸነፈው ግልሰብ ገንዘቡ እንዲሰጥ ያዛል።

## ገንዘቤ እንዳይቆረጥብኝ ወይም እንዳይቀነስብኝ መከላከል እችላለሁኝ?

**ሊሆን ይችላል።** አንዳንድ የገንዘብ ዓይነት በሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፣ ነገር ግን እንዳይወሰዱ ለማድረግ አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይገባዎታል። የሚቀጥለው ገጽ ላይ እንዳይነኩ ለማድረግ የሚችሏቸው የገንዘብ ዓይነቶች ዝርዝር ይመልከቱ። ገንዘብ ጥበቃ እንደሚደረግበት እና እንደማይደረግበት የመወሰን ስልጣን የዳኛው ነው።

የተወሰኑ ዓይነት የመንግስት ድጎማዎችን (ልክ እንደ ማህበራዊ ደህንነት ያሉ)፣ የእርስዎ ባንኩ በራሱ አስቀድሞ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። ስለዚህ ለማወቅ ለባንክዎ ስልክ ይደውሉ።

## ገንዘቤ እንዳይወሰድብኝ እንዴት መከላከል እችላለሁኝ?

"Motion to Exempt (Protect) Funds and Request for Hearing" ["ከተቆራጭ ነፃ ገንዘብ አቤቱታ ያቅርቡ እና ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲታይሎት ይጠይቁ"]።

እነዚህ 2 ቅደም ተከተሎች ይኖራቸዋል፡-

1) **"Motion to Exempt (Protect) Funds and Request for Hearing" ["ከተቆራጭ ነፃ ገንዘብ አቤቱታ እና በችሎት ይታይልኝ" ቅጽ ይምሉ"]።** *ቅጹ በዚህ ደብዳቤ መጨረሻ ላይ ዓባሪ ተደርጓል።*

2) በተቻለ መጠን ለፍርድ ቤቱ ቅጹን ሞልተው ይስጡ።
   ምንም እንኳን ጥበቃ የሚደረግለት ቢሆንም፣ ብዙ ከቆዩ፣ ገንዘብዎን ሊያጡ ይችላሉ፣ ።

በተጨማሪም በእርስዎ ላይ ክስ የመሰረተብዎን ድርጅት (ወይም ጠበቃውን) ጋር መደወል ይችላሉ።  ገንዘብዎ *ከተቆራጭ ነፃ* እንደሆነ ያስረዷቸው። ገንዘብዎን እንዲለቀቅሎት ይጠይቋቸው። ገንዘብዎ ከመቆረጥ ነፃ እንደሆነ ለማስመስከር ማስረጃ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

## ይሄንን አቤቱታ እንዴት ማቅረብ እችላለሁኝ?

ከሚከተሉት አንዱን መንገድ በመከተል አቤቱታውን ማቅረብ ይችላሉ፦

1. በፍርድ ቤት ውስር **በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሰራተኛ ቢሮ** ውስጥ **በአካል በመገኘት** ክስ ማቅረብ ይችላሉ። አድራሻው፦ Building B, 510 4th Street, N.W., Room 120, Washington, D.C. 20001.
2. በፍርድ ቤቱ ድረገጽ በኩል **ኦንላይን** አቤቱታውን ያቅረቡ፦ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing
3. ሰነዱን **በደብዳቤ** በዚህ ይላኩ Superior Court of the District of Columbia, Small Claims Clerk's Office – Room 120, 510 4th Street, N.W. Washington, D.C. 20001

## ይሄንን አቤቱታ ማቅረብ ገንዘብ ያስከፍላል?

አዎ። ይሄንን አቤቱታ ለማቅረብ **$10** ዶላር ክፍያ አለው። መክፈል የማይችሉ ከሆነ፣ (*ፎርማ ፓውፐሪስ [in forma pauperis]* ተብሎ የሚጠራ) ቅጽ በመሙላት **ይሄ ክፍያ እንዲነሳሎት** ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ይሄንን ቅጽ ኦንላይን በዚህ አድራሻ https://www.dccourts.gov/services/forms ላይ በመሄድ ወይም በ (202) 879-1120 ስልክ ላይ በመደወል ማግኘት ይችላሉ። ይሄ አቤቱታ የቀረበበት **ተመሳሳይ ጊዜ ላይ** ከክፍያ ነፃ ቅጽን አያይዘው ያቅርቡ።

## የእኔን ገንዘብ እንዳይነካ ለማድረግ የፍርድ ቤቱን ቅጽ ሞልቼ አስገብቼአለው። ቀጥሎ ምን ይፈጠራል?

ቅጹን ሞልተው ካስገቡ በኋላ፣ ፍርድ ቤቱ የሰሚ ችሎት ቀነ ቀጠሮ ይሰጣል። ሁለት ነገሮችን ማድረግ ያስፈልጎታል።

1. **ሰነዶችዎን ያዘጋጁ።** ገንዘብዎ ጥበቃ እንደሚደረግለት የሚያሳዩ ሰነዶችን ማምጣት አለብዎ። *የሚቀጥለው ጥያቄ ላይ ምን ዓይነት ገንዘቦች ጥበቃ እንደሚደርግላቸው ይወቁ።*
2. **ችሎቱ በሚሰማበት ቀን ላይ በአካል ይገኙ።** ምንም እንኳን ገንዘብዎ ጥበቃ የሚደረግለት ቢሆንም፣ ፍርድ ቤት የማይገኙ ከሆነ፣ ገንዘብዎን ሊያጡ ይችላሉ፣ ።

## ምን ዓይነት ገንዘብ ጥበቃ ይደረግለታል?

በአብዛኛው ጥበቃ የሚደረግላቸው የገንዘብ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- የማህበራዊ ደህንነት ጡረታ ገንዘብ (Social Security retirement)፣ ተጨማሪ የማህበራዊ ደህንነት ድጎማ (Supplemental Social Security [SSI])፣ ወይም ማህበራዊ ደህንነት የአካለስንክሉነት ኢንሹራንስ (Social Security Disability Insurance [SSDI])
- የስራ አጥነት ድጎማዎች
- የሕዝብ ድጎማ / TANF ጥቅማጥቅሞች
- የፌደራል ሲቪል አገልግሎት የጡረታ ጥቅማጥቅሞች
- የጡረታ መሰናበቻ፣ ጡረታ እና ዓመታዊ ዕቅድ ክፍያዎች

- የቀድሞ ሰራዊት አባላት ድጎማዎች
- የሠራተኞች ካሣ
- የቀለብ፣ ተቆራጭ ገንዘብ ፣ ወይም የተለየ ድጎማ ገንዘብ
- በሲቪል ወይም በወንጀል ክስ ላይ በፍርድ ቤት የተፈረደ ገንዘብ
- ቤትዎ የራስዎ ከሆነ ማንኛውም እስከ $850 ዶላር የሚሆን ገንዘብ።
- ቤትዎ የራስዎ **ካልሆነ** ማንኛውም እስከ $8,925 ዶላር
- የሚሆን ገንዘብ።

ዝርዝሩ ሁሉንም የሚያካትት አይደለም። ለተጨማሪ መረጃ የዲሲ ሕገ ደንብ § 15-501(a) ይመልከቱ። በተጨማሪም አንዳንድ ጥበቃ የሚደረግላቸው ገንዘቦች ሊገደቡ ይችላሉ፣ እና የቀለብ ተቆራጭ ወይም የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ የሚከፍሉ ከሆነ ጥበቃዎቹ ላይሰሩ ይችላሉ።  ጠበቃ ማነጋገር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## የሕግ እገዛ እንዴት ማግኘት እችላለሁኝ?

በዚህ ሂደት ላይ ለመግባት ጠበቃ አያስፈልጎትም፣ ነገር ግን ጠበቃ ለማነጋገር የሚፈልጉ ከሆነ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ላይ ኦንላይን እንዴት ነፃ የሕግ እገዛ ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት ይችላሉ አድራሻው https://www.dccourts.gov/services/represent-yourself ነው።

እስካሁን ድረስ ስለ ክሱ ምንም ያልሰሙ ከሆነ፣ ጠበቃ ሊያስፈልጎት ይችላል። እንደ ሁኔታው፣ ፍርድ ቤቱ የወሰነውን ውሳኔ እንዲቀለብስ የይግባኝ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

## ተጨማሪ ጥያቄዎች ያሉኝ ከሆነ ምን ማድረግ እችላለሁኝ?

የአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች እና የማስታረቅ ቅርንጫፍ ቢሮ የፍርድ ቤት ሰራተኛን ወይም የሌላ ሲቪል ዲቪዝዮን የፍርድ ቤት ሰራተኛ ቢሮን ማነጋገር ይችላሉ።